# ሐዘን እና ትካዜ በቃ

# وداعاً للهموم والأحزان


لفضيلة الشيخ الدكتور

عبد السلام بن محمد الشويعر

ዝግጅት፡ ሸይኽ ዐብዱሰላም ኢብኑ ሙሐመድ አሽ-ሹወይዒር




ትርጉም፡ ሁብዬ ሰዒድ

بسم الله الرحمن الرحيم

ምስጋና ሁሉ ለአላህ የተገባ ነው። የአላህ ውዳሴ፣ ሰላም እና በረከት በነብያችን ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸው፣ መንገዳቸውን በተከተለ፣ በፈለጋቸው በተመራ፣ ሱናቸውን በተከተለ እና እስከ ቂያማ ቀን ድረስ ቀናውን መንገድ በተከተለ ላይ ሁሉ ይሁን።

ከዚህ በመቀጠል፡

የተከበራችሁ ወንድሞች ሆይ! የዛሬው ንግግራችን ጊዜው አጭር፣ ነገር ግን ወደ ብዙ ቅርንጫፎች ስለሚከፋፈል ጉዳይ ነው። የዛሬው ንግግራችን በሁላችንም ላይ የሚከሰት ጉዳይ ነው። በህጻናችን በትልቆቻችን፣ በወንዶቻችንም በሴቶቻችን፣ በሃብታምም በድሃም፣ በመሪም በተመሪም የሚከሰት ነው። ጉዳዩ ሰለ ነፍሳችንና ለሷም ሰለሚከሰተው **ሐሳብ** እና **ትካዜ** ነው። ሐሳብ እና ትካዜ አላህ ﷿ በኣደም ልጆች ላይ የጻፋቸው ጉዳዮች ናቸው። ለዚህም አቡ ዳውድ እና ቲርሚዚይ ላይ እንደ ተዘገበው ነብዩ ﷺ እንዲህ በለዋል፡

«إن أصدق الأسماء عند الله ﷿ الحارث والهمام»

**«አላህ ﷻ ዘንድ ይበልጥ እውነተኛ ስሞች የሆኑት *አል-ሓሪሥ* (አራሹ) እና *አል-ሀማም* *(አሳቢው)* ናቸው።»** የኢስላም ምሁራንም የሚከተለዉን ብለዋል፡ *“እነኚህ ሁለት ስሞች እውነተኛ ስም ናቸው የተባሉበት ምክንያት የትኛውም የሰው ልጅ እርሻ የሚያርስ ወይም ከሃሳብ የሆነ ነገር የሚያጋጥመው መሆኑ ስለማይቀር ነው።”* ለዚህም **አል-ሀማም** የሚለው የኣደም ልጆች ስም አላህ ﷿ ዘንድ እውነተኛ ከሆኑት ስሞች አንዱ ነው

የተባለው። ከሰዎች ውስጥ በእርሱ ላይ የሞት ሐሳብ ወይም የመልካም ነገሮች ማምለጥ ወይም ከመልካም ነገሮች እንዳያመልጠው የሚፈራው ነገር በማምለጡ የሚተክዝ ቢሆን እንጂ አይገኝም። *ሐዘን (ትካዜ) ባለፈ ጉዳይ ላይ ማዘን ወይም መተከዝ ሲሆን፤ ሀም (ሐሳብ) ደግሞ ወደፊት ሊመጣ ስለሚችል ነገር መጨነቅ ነው።*

የተከበራችሁ ወንድሞች ሆይ! ሐሳብ በአላህ ﷻ ነብያትና በምርጥ ባሮቹም ላይ በርግጥም ተከስቷል። ይሄውና ነብይ የነብይ ልጅ እና የነብያት አባት የሆኑት “የዕቁብ” ﷺ እንዲህ እንዳሉ አላህ ﷻ በቁርኣኑ ነግሮናል፡

﴿ إِنَّمَآ أَشْكُواْ بَثِّي وَحُزْنِيٓ إِلَى ٱللَّهِ ﴾ [يوسف:86]

*﴿ጭንቀቴንና ሐዘኔን ወደ አላህ ብቻ ስሞታ አቀርባለሁ።﴾* [ዩሱፍ ፡ 86]

ኑሕም ﷺ ልጃቸው ባመጸባቸው ጊዜ ሐሳብ አጋጥሟቸው ነበር። ኢብራሂምም ﷺ አባታቸው በእርሳቸው ላይ ያሳዩትን ጭካኔ አይተዋል። አዩብም ﷺ በሰውነታቸው (ታመው) ተፈትነዋል። ሉጥም ﷺ በእንግዶቻቸው ላይ ተረብሸዋል፤ ባለቤታቸውም እሳቸው ይዘውት በመጡት መልእክት ክዳለች። ሙሐመድም ﷺ ለሌላ ለማንም ያላጋጠመ ሐሳብ አጋጥሟቸዋል።

ነብዩ ﷺ ከሐሳብ የተነሳ ወደየት አቅጣጫ መሄድ እንዳለባቸው ማወቅ እስከሚሳናቸው ድረስ ከባድ ሐሳብ አጋጥሟቸው ነበር። ሰሒሑል-ቡኻሪ ላይ ከእናታችን ዓኢሻ እንደተዘገበው ነብዩን ﷺ እንዲህ ብላ እንደጠየቀች ትናገራለች፡ *“በአንተ ላይ ካለፉት ቀናት ከባዱ ቀን የትኛው ነው?”* እርሳቸውም *«በእኔ ላይ ካለፉት ከባዱ ቀን ነፍሴን በዐብዱያለይል' ልጅ ላይ ባቀረብኩ ጊዜ ኢስላምን*

[1] ዐብዱያለይል ኢብኑ ዐምር አሥ-ሠቀፊይ ከሠቂፍ ጎሳ መሪዎች አንዱ ሲሆን ከነብዩ ﷺ ጋር ያለው ታሪክ በእጅጉ የጠቀረ ነው። ታሪኩም ነብዩ ﷺ አጎታቸው አቡ ጧሊብ ከሞቱ በኋላ መካ ውስጥ ያሉት የደዕዋ በሮች በሙሉ ተዘጉባቸው። ይህን ጊዜ ነበር ነብዩ ﷺ የሠቂፍን ጎሳ ወደ ኢስላም ለመጥራትና ረዳት እና አጋዥ እንዲሆኗቸው በመከጀል ወደ ጧኢፍ ያመሩት። ጧኢፍ ሲደርሱም ከሠቂፍ ጎሳ መሪዎች ጋር ተገናኙ። ከነዚህ መሪዎች መካከል ደግሞ ዐብዱያለይል ኢብኑ ዐምር አንዱ ነበር። በዚህ

*አልቀበልም ባለ ጊዜ ነው።»* ከዛም ቀጥለው: *«ወደ ፊትለፊቴ እየተጓዝኩ ወደ ፄት አቅጣጫ መሄድ እንዳለብኝ አላውቅም ነበር።»* አሉ። በዛ ጊዜ ነብዩ ﷺ በጣኢፍ መንገድ ላይ ቀርን አሥ-ሠዓሊብ የሚባል ስፍራ በደረሱ ጊዜ ከራሳቸው በላይ ዳመና አጠለላቸው። በዛን ጊዜ ሲመለከቱ ጂብሪልን እና ከእርሱ ጋርም የጌታውን ትእዛዝ የያዘ የተራሮች መልኣክን ተመለከቱ፤ በዚህ ወቅት መልኣኩ በሰዎቹ ላይ ሁለቱን ተራሮች ለማላተም የነብዩን ﷺ ፍቃድ ጠየቀ። ነገር ግን ነብዩ ﷺ እዝነታቸው አሸነፈች እና በነዛ ሰዎች ላይ ሁለቱን ተራሮች እንዳያ ላትማቸው ከለከሉት።

ስለዚህ ወንድሞች ሆይ! ከዚህ ሐዘን እና ትካዜ ሰላም የሚሆን አንድ ሰው እኳን ቢኖር ኖሮ የአላህ ﷻ ነብያት እና መልካም ባሮቹ እና ወዳጆቹ ሰላም ይሆኑ ነበር። ነገር ግን አንድም ሰው ከዚህ ነገር አልዳነም። ለዚህም አንድ አማኝ ከዚህ ሐሳብ እና ትካዜ የሆነ ነገር ባጋጠመው ጊዜ ሌሎቹን ነገሮች በሚያከምበት መንገድ አይደለም ይህን የሚያክመው። አንድ ሙስሊም ሐዘንና ትካዜ ባጋጠመው ጊዜ እርሱ በዚህ ሐሳብ እና ትካዜ የጊዜው ብቸኛና የዘመኑ ተነጣይ እንዳልሆነ ማወቅ አለበት። እንዲያውም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሀብታምም ይሁን ድሃ፣ መልካምም ይሁን አመጸኛ ያላጋጠመው አይገኝም። ጌታችን አላህ ﷻ እንዲህ ይላል:

﴿ إِن تَكُونُواْ تَأۡلَمُونَ فَإِنَّهُمۡ يَأۡلَمُونَ كَمَا تَأۡلَمُونَۖ وَتَرۡجُونَ مِنَ ٱللَّهِ مَا لَا يَرۡجُونَۗ وَكَانَ ٱللَّهُ عَلِيمًا حَكِيمًا﴾ [النساء: 104]

---

ጊዜ ነብዩ ﷺ ያላሰቡት ነገር ገጠማቸው። በማክበር እና ጥሪያቸውን በመቀበል ፈንታ ነብዩን በማዋረድ እና በእርሳቸው ላይ በመሳለቅ ሰዎችን ከአላህ መንገድ ከለከሉባቸው። ይባስ ብሎም የሰፈሩን ህጻናትና የአካአቢዉን ቂላቂሎች በነብዩ ﷺ እና በባልደረባቸው ዘይድ ኢብኑ ሐሪሣ ላይ አነሳሱባቸውና እንዲያባርሯቸው አደረጉ። ይህ ክስተት በነብዩ ነፍስ ላይ እጅግ ከባድ የሆነ ሐሳብና ትካዜን ያመጣባቸው ነበር።

﴿(ስትቆስሉ) የምትታመሙ ብትሆኑ እናንተ እንደምትታመሙት እነሱም ይታመማሉ። (እነሱ) የማይከጅሉትንም ከአላህ ﷻ ትከጅላላችሁ። አላህም አዋቂ ጥበበኛ ነው። ﴾ [አን-ኒሳእ፡ 104]

አማኝ እና ከሃዲ በሐሳብም ሆነ በሌላ ህመም እኩል ናቸው። ነገር ግን አማኝ የሆነ ሰው ከነዚህ ነገሮች (ህመሞች) አንዳች ነገር ቢያጋጥመው በተለያዩ ነገሮች ያክመዋል። ይህንንም ነገር (ህመም) አማኝ ያልሆኑ ሰዎች በሌላቸው ነገሮች ይቆጣጠረዋል።

## አንድ አማኝ ሐሳብ ወይም ትካዜ ባጋጠመው ጊዜ በነብዩ ﷺ ሱናህ በመጡት መድኃኒቶች ያከማቸዋል። እነሱም የሚከተሉት ነጥቦች ናቸው፡

**የመጀመሪያው ነጥብ፡ በአላህ ﷻ ውሳኔ (ባለፈውም ወደፊት በሚመጣውም) ማመን።**

ጠበራኒይ በዘገቡት ሐዲሥ ነብዩ ﷺ እንዲህ በለዋል፡

« الإيمان بالقضاء والقدر يزيل الهم والحزن »

*« በአላህ ﷻ ውሳኔ ማመን ሐሳብና ትካዜን ያስወግዳል።»*

ይህም የሆነው አንድ አማኝ ከሐሳብና ትካዜ አንዳች ነገር ባጋጠመው ጊዜ ያመለጠው ነገር በአላህ ﷻ ውሳኔ እንደሆነ ያስታውሳል። በሰሳች ስስትና በከልካይ ክልከላ እንደማይመለስም ያምናል። ለዚህም ነብዩ ﷺ እንዲህ በለዋል፡

«لا تقل لو فعلت لكان كذا وكذا، فإن لو تفتح عمل الشيطان»

*« ይህን ባደርግ ኖሮ እንዲህ አይሆንም ነበር አትበል፣ (ቢሆን ኖሮ) የምትለው ቃል ለሸይጣን ስራ በር ትከፍታለች።»*

አንድ ሰው በሰውነቱ ላይ ጉዳት ሲደርስበት፣ ወይም ወዳጁን ሲያጣ፤ ወይም በዱንያ ላይ አንድ አጋጣሚ መጥቶ ገንዘቡን ቢያጠፋበት፣ ይህን አላህ ﷻ እንደጻፈው ያውቃል። ከእርሱ በፊት አላህ ﷻ የሚያውቀው፣ የወሰነውና የፈለገው ነገር እንደሆነም ያምናል። ይህ

በአላህ ﷻ  ውሳኔ ማመኑ ደግሞ ነፍሱን ትርፋማ ለማድረግ ምክኒያት ይሆነዋል፤ ነፍሱ ከተከሰተባት ሐሳብም እንድታርፍ ያደርጋታል።

ወደፊት ስለሚመጣው ነገር ማሰብ ከሆነ ደግሞ፣ አማኝ ወደፊት ስለሚመጣው አይጨነቅም። ምክንያቱም ይህ ነገር በአላህ ﷻ እውቀት የተወሰነ መሆኑን፣ እኛ የምንሰራቸው ስራዎች ምክንያቶች (ሰበቦች) ብቻ እንጂ ሌላ እንዳልሆኑ ያውቃል። ለዚህም አማኝ በአላህ ﷻ ውሳኔ ያምናል። ከዛሬው ይልቅ በነገው ይደሰታል። በእርግጥም ነብዩ ﷺ ተፋኡል ያስደሰታቸው ነበር፤ ወደፊት ለሚመጣውም ተፋኡል ያደርጉም ነበር። ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲሥ ነብዩ ﷺ እንዲህ አሉ፡

«إن للشيطان بابن آدم لمة، وللملك بابن آدم لمة، فأما لمة الشيطان فإنه يحزنه...»

***«ለሸይጣን በኣደም ልጆች ላይ ቅርበት አለው፤ መልአክም በኣደም ልጆች ላይ ቅርበት አለው።»*** ከዛም አስከትለው ነብዩ ﷺ አሉ፡ ***«የሸይጣን ቀርበት ሰውየውን ያስተክዘዋል።»***

ወደፊት በሚመጣው ያስተክዝሃል፤ ሸይጣን ብዙ ጊዜ ወደ ኣደም ልጅ ይመጣል፤ ብዙ ጊዜያትም ወደ እርሱ ይቀርባል፤ ባለፈው ነገር እንዲያዝን ያደርገዋል፤ ወደፊት በሚመጣውም ያስፈራራዋል። ሸይጣን ወደርሱ የቀረበው ሰው ነገ በሚሆነው ነገር ሲፈራ ታየዋለህ። ምናልባትም ገና ሳያገባ በልጁ ላይ ይፈራል፤  በሙሉ ጤና ላይ ላይ ሆኖ ሳለ ስለጤናው ሲጨነቅ ትመለከተዋለህ፤ ስለ ሽምግልና ጊዘው እና በዛን ጊዜ ምን እንደሚሚያጋጥመው ሲያስተነትን ታየዋለህ፤ ንግዱ ትርፋማ ሆኖ ሳለ በገንዘቡ ላይ ይፈራል። ይህ ሁሉ እሱን ሊያስትክዘው፣ ሐሳቡንና ጭንቀቱን ሊጨምርበት ከሸይጣን የመጣ ነገር እንጂ ሌላ አይደለም። ነገር ግን አማኝ የሆነ ሰው የሚመጣው ነገር ሁሉ በአላህ ﷻ ውሳኔ እንደሆነ፣ ይህም ሐሳብ የዛሬውን የሚያበላሽ እንዲሁም የነገውን የማያስተካክል እንደሆነ ያውቃል። በዛሬ ቀን ለነገው የተጨነቀ ሰው እውነታው የዛሬውን ማበላሸቱና የነገውም አላህ ﷻ ለእርሱ ከጻፈለት ምንም ነገር አለመቀየሩ ነው። በተወሰኑ ጋዜጦች ላይ እንደተጠቀሰው አንድ ሰው ኢንግላንድ (England) አገር ውስጥ ከሃያ አምስት አመት

በፊት አንድ ጥናት ሰርቶ ነበር። እሱም ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች ዘንድ መጣና ከመቶ ተማሪዎች በላይ ሰብስቦ *"ነገ ምን መሆን ተፈልጋላችሁ?"* ብሎ ጠየቀ። ሁላቸውም የወደፊታቸወን አሰመሩለት፤ የህይወት ጉዞዋቸውንም ወሰኑለት ከዛ ከሃያ አመት ገደማ በኋላ እነዛን ሰዎች ለማግኘት ሞከረ። ከነሱም ወደ 70% የሚሆኑትን እንጂ አላገኘም ነበር። የተቀሩትን 30% የሚያገኝበት መንገድ አላልገኘም። በህይወት ላይኖሩም ይችሉ ይሆናል ወይም በሌላ ምክንያት ጠፍተው ሊሆን ይችላል። ከነዛ ከቀሩት 70% ደግሞ መጀመሪያ ባሰመሩት መንገድ ላይ ያገኛቸው ከ3% የማይበልጡ ነበሩ። የሌሎቹ ህይወት እነሱ (ከ20 ዓመት በፊት) ቀድመው ካሰመሩት አቅጣጫ ውጭ ሆኖ አገኘው። ይህ ጥናት ለሌላ ጉዳይ ላይ የተጠና ቢሆንም እኛ ያለንበትን ተጨባጭ ያሳየናል። አንተ በነገህ ላይ ምንም ያክል ብትሰስት ነገህ በአላህ ﷻ ውሳኔ የሚሆን ነው። አንተ የአቅምህን ሰበብ አድርስ የሩቅ እውቀት አላህ ﷻ ዘንድ ነው።

**ሁለተኛው ነጥብ፡ አላህን ﷻ በመለመን (ዱዓ በማድረግ) ያንን ሐሳብ ማባረር።** ነብያችን ﷺ አላህ ሐሳብና ትካዜያችውን እንዲያነሳላችው ዱዓ ያበዙ ነበር። ሰሒሑል-ቡኻሪ ላይ እንደተዘገበውና አነስ ኢብኑ ማሊክ ﵁ እንደተናገረው *"ነብዩ ﷺ ሰምንት አመት ተንዳኝቻቸዋለሁ ብዙ ጊዜ የሚያዘወትሩት ዱዓእ **«ጌታዬ ሆይ ከሐሳብና ከትካዜ በአንተ እጠበቃለሁ።»** የሚል ነበር"* ይላል። አንድ ሰው ወደ አላህ ﷻ እጆቹን ከፍ አድርጎ አይጠራውም፣ ወደ እርሱም አይዋደቅም፣ ሚስጥሩንም ወደ እርሱ ስሞታ አያቀርብም፣ አላህ ﷻ ሃሳቡን የገላገለው፣ ጭንቀቱንና ያስቸገረውን ነገር ሁሉ ያስወገደለት ቢሆን እንጂ። አላህ ﷻ እንዲህ ይላል፡

﴿أَمَّن يُجِيبُ ٱلْمُضْطَرَّ إِذَا دَعَاهُ وَيَكْشِفُ ٱلسُّوٓءَ وَيَجْعَلُكُمْ خُلَفَآءَ ٱلْأَرْضِ ۗ أَءِلَٰهٌ مَّعَ ٱللَّهِ ۚ قَلِيلًا مَّا تَذَكَّرُونَ﴾ [النمل: 62]

﴿*ወይም ያ ችግረኛን በቸገረው ጊዜ ሲለምነው የሚቀበል፣ መከራንም የሚያስወግድ፣ በምድር ላይም ምትኮች የሚያደርጋችሁ (ይበልጣልን ወይስ የሚያጋሩት)? ከአላህ ሌላ ሌላ አምላክ አለን? ጥቂትም አትገሰጹም?*﴾ *[አን-ነምል፡ 62]* ያችሁ እሱ አላህ ﷻ ነው።

ከነብዩ ﷺ የሚከተለው ንግግር በትክክለኛ ሰነድ ተላልፏል፡

*«ነገሩ የአላህን ውሳኔ ዱዓ እንጂ አይመልሰውም።»* በአንተ ላይ ምንም አይነት ሐሳብ ቢመጣብህ፣ አንድን ነገር ምንም ያክል ብትፈራ፣ አላህን በልመናህ እውነተኛ ሁነህ፣ በሱም ላይ መልካም ጥርጣሬን አሳድረህ ከለመንከው አላህ ﷻ ከአንተ ላይ ሐሳብህንና ጭንቀትህን ያስወግድልሃል።

## ሶስተኛው ነጥብ፡ የአላህን መጽሐፍ (ቁርኣን) ማንበብን ማብዛት።

ነብያችን ከሐሳብ እና ከትካዜ የሆነ ነገር ባጋጠማቸው ጊዜ ቢላልን ጠርተው *«ቢላል ሆይ! በሰላት አሳርፈን»* ይሉ ነበር። ኢማሙ አድ-ዳሪሚይ ዘንድም ነብዩ ﷺ *« ፋቲሓ ውስጥ ለሰባ በሽታ የሚሆን መድሓኒት አለ። (ከበሽታዎቹ) ቀላሏ ሐሳብ ነች።»* ይሉ እንደነበር ተዘግቦልናል። አንድ ሰው ይችን ትልቅ፣ የአላህን መጽሓፍ መክፈቻ መዕራፍ ማንበብ ባዘወተረ ጊዜ፣ በተለይ ሰላት ውስጥ ከሆነ፣ አላህ ﷻ በነፍሱ ውስጥ ያለውን ሐሳብ እና ጭንቀት ያስወግድለታል። ኢብኑ ሒባን፣ ኢማሙ አሕመድና ሌሎችም ጋር እንደተዘገበው፣ ነብዩ ﷺ ባልደረቦቻቸወን ዱዓ ሲያስትምሩ፡ *« (ዱዓዉን) የሰማው ሰው ይሸምድደው።»* አሉ። በዛ ዱዓ ውስጥም የሚከተለውን አወሱ፡

« اللهمّ إني أسألُك بكلِّ اسمٍ هو لك سميتَ به نفسَك أو أنزلتَه في كتابِك أو علمته أحدًا من خلقِك أو استأثرت به في علمِ الغيبِ عندك ، أن تجعلَ القرآنَ العظيمَ ربيعَ قلبي ونورَ صدري وجلاءَ همّي وحزني»

*« አላህ ሆይ! ለአንተ በሆነው ስም ሁሉ፣ አንተ ራስህን በሰየምክበት፣ ወይም በመጽሐፍህ ውስጥ ባወረድከው፣ ወይም ከፍጡራንህ ለአንዱ ባስተማርከው፤ ወይም አንተ ዘንድ ከሩቅ እውቀቶች እንዲሆን በመረጥከው ስምህ ቁርኣንን የልቤ ብርሃን እንደታደርገው እና የሐሳቤና የትካዜዬ ማስወገጃ እንድታደርገው እለምንሃለሁ»* ከዛም ቀጠሉና፡ *« አላህ ﷻ ሐሳቡን እና ጭንቀቱን ያስወግድለታል።»* አሉ።

**ቁርኣን የሐሳብና የትካዜ ማስወገጃ ምክንያት ለምን ሆነ?** ምክንያቱም አላህ ﷻ ቁርኣንን መድኃኒት አድርጎታል። እሱም ለአካላዊና ለነፍስ በሽታዎች መድኃኒት ነው። ሐሳብና ትካዜ ደግሞ በሰው ልጆች ላይ ከሚከሰቱት የነፍስ በሽታዎች እንደሆኑ ጥርጥር የለውም። አንድ ሰው የአላህን ቁርኣን ካነበበና ካመነበት አላህም ﷻ ሐሳቡን እና ጭንቀቱን ያስወግድለታል። ቁርኣን በውስጡ ከእኛ በፊት ያለፉትን ሰዎች ዜና እና ከእኛ በኋላ የሚመጡትን ሰዎችም ወሬ የያዘ ነው። ኢማሙ አት-ቲርሚዚ ከዐሊይ ኢብኑ አቢ ጧሊብ ይዘው እንደዘገቡት *"የአላህ መልእክተኛ ባልደረቦች ትንሽ መሰላቸት ባጋጠማቸው ጊዜ የአላህ መልክትኛ ሆይ! ተርክልን በለው ይጠይቃሉ"* ከዛም አላህ ﷻ የሚከተለውን አንቀጽ አወረደ፡

﴿نَحْنُ نَقُصُّ عَلَيْكَ أَحْسَنَ ٱلْقَصَصِ بِمَآ أَوْحَيْنَآ إِلَيْكَ هَٰذَا ٱلْقُرْءَانَ﴾ *[ يوسف:86]*

*﴿እኛ ይህንን ቁርኣን ወደ አንተ በማውረዳችን በጣም መልካም ዜናዎችን በአንተ ላይ እንተርካለን﴾ [ዩሱፍ፡ 86]* ከዛ ሌላ ጊዜም ድካም ሲያጋጥማቸው *"የአላህ መለክተኛ ሆይ! ኣውራን"* ማለትም በነፍሶቻችን ውስት ያለውን ችግር የምናስወግድበት እና መሰላቸታችንን የምናጠፋበትን ወሬ አውራን ባሉ ጊዜ አላህም ﷻ የሚከተለውን አወረደ፡

﴿ٱللَّهُ نَزَّلَ أَحْسَنَ ٱلْحَدِيثِ كِتَٰبًا مُّتَشَٰبِهًا مَّثَانِيَ﴾ *[الزمر: 23]*

*﴿አላህ ከዜና ሁሉ መልካምን፣ ተመሳሳይ፣ ተደጋጋሚ የሆነን መጽሐፍ አወረደ።﴾ [አዝ_ዞመር፡ 23]*

ይህ የሚያመላክተው የአላህን መጽሐፍ ማንበብና መልክቶቹንም ማጤን በአላህ ﷻ ትእዛዝ ሐሳብን፣ ትካዜና መሰላቸትን ለማስወገድ ሰበብ እንደሆነ ነው፡፡

## አራተኛው ነጥብ፡ ለአንድ ሰው በአላህ ﷻ መንገድ ላይ የተወዳጀው እና ስሞታውን የሚነግረው ወንድም ሊኖረው የገባል፡፡

አንድ ሰው ለእርሱ ዜናውን የሚነግረው፣ በውስጡ ያለውን ጭንቀት ያመጣበትን ምክንያት የሚያወያየው ወንድም ሊኖረው ይገባል፡፡ አቡ ነስር አልፊርያቢይ ታዋቂው ሙስሊም ተመራማሪ *"በአብዘሃኛው በውስጣችን ያለውን ሐሳብ የምናወጣበት መንገድ ንግግር ማብዛት ነው፡፡"* ሰውዬው ብዙ ሐሳቦች ያሉትና ብዙ የሚያስተነትን ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ወንድሙን ባናገረው ጊዜ፣ በውስጡ ያለውን ለጓደኛው ባወራው ጊዜ፣ በውስጡ ያለው ነገር ቀላል እንደሆነ ይረዳል፡፡ በዛም ምክንያት የመጣበት ሐሳብና ጭንቀት መምጣት እንደሌለበት ይገነዘባል፡፡

ለዚህም አላህ ሙሳን ﷺ ወደ ፊርዐውንና ወደ ህዝቦቹ እንዲሄዱ ባዘዛቸው ጊዜ፣ ሙሳም ﷺ ወንድማቸውን ረዳት እንዲያደርግላቸው አላህን ለመኑ፡፡ ሙሳም አላህ ﷻ የሰጣቸው ትእዛዝ ከባድ መሆኑን ሲገነዘቡ አላህን የተማጸኑበትን ታሪክ እንዲህ ይነግረናል፡

﴿قَالَ رَبِّ ٱشْرَحْ لِي صَدْرِي ۝٢٥ وَيَسِّرْ لِيٓ أَمْرِي ۝٢٦ وَٱحْلُلْ عُقْدَةً مِّن لِّسَانِي ۝٢٧ يَفْقَهُوا۟ قَوْلِي ۝٢٨
وَٱجْعَل لِّي وَزِيرًا مِّنْ أَهْلِي ۝٢٩ هَٰرُونَ أَخِي ۝٣٠ ٱشْدُدْ بِهِۦٓ أَزْرِي ۝٣١ وَأَشْرِكْهُ فِيٓ أَمْرِي ۝٣٢﴾

*[طه: 25-32]*

*﴿ሙሳም አለ "ጌታዬ ሆይ! ልቤን አስፋልኝ፡፡" ነገሬንም ለኔ አግራልኝ፡፡ ከምላሴም መኮላተፍን ፍታልኝ፡፡ ንግግሬን ያውቃሉና፡፡ ከቤተሰቦቼም ለእኔ ረዳትን አድርግልኝ፡፡ ሃሩንን ወንድሜን፡፡ ኃይሌን በእርሱ አበርታልኝ፡፡ በነገሬም አጋራው፡፡﴾* *[ጣሃ፡ 25-32]*

ለሙሳ ﷺ አላህ ﷻ ረዳት የሚሆን ወንድም እንዲያደርግላቸው እንደተማጸኑት አላህ

ﷺ ነግሮናል። አንድ ሰው እውነተኛ ወንድምና መካሪ ካለው፣ በእርሱ ላይ አላህ ﷻ ከዋላቸው ጸጋዎች አንዱ ነው። በዚህ ጊዜ እንዲህ አይነት ጓደኛ የመገኘቱ እድል የጠበበ ቢሆንም። አቡ ኑዐይም [ሒልየቱል-አውሊያእ] ላይ እንደዘገቡት ነብዩ ﷺ ***«አራት ነግሮች (የተሰበሰቡለት) እድለኛ ነው።»*** አሉ። እነዚህ አራት ነገሮች የተሰበሰቡለት የእውነትም በዚች ምድር ላይ እሱ ነው እድለኛ፤ ከነዚህ አራት ነገሮች ***«እውነተኛ ወንድም»*** ወይም ***«እውነተኛ ጓደኛ»*** ብለው ተናገሩ። ይህ ሐዲሥ አንድ ሰው ጓደኛ እንደሚያስፈልገው ያመላክታል። ለአላህ ብሎ የተወዳጀውና ሚስጥሩንና ነገሩን የሚያጋራው ወንድም ማግኘት ሌላ ጸጋ የማይወዳደረው ታላቅ ጸጋ ነው። በዚህ ዘመን ሁሉም ነገር የሚሸጥና የሚገዛ በሆነበት ጊዜ፣ ስሞታ የሚነገረውም ሰው በገንዘብ ሆኖዋል የሚነገረው። ነፍስን የሚያከመው ሰው ከታማሚው ጋር ረጂም ሰዓት ይቀመጣል፤ የሚቀመጠው ስሞታውን ለማዳመጥና ምን እንደሚሰማው ለመመልከት ብቻ ነው። ከዛ በኋላ (ታማሚው ሐሳቡን ሰለተካፈለው ብቻ) ደስተኛ ሆኖ ይመለሳል። ሰውየው ስሞታውን በህመሙ ለሚታመምለት እና በትካዜው ለሚተክዝለት ወንድሙ ቢሆን የነገረው ይህ ታላቅ ነገር ነበር።

ላለማዘን፤ ለመጽናናት፣ ለመደሰት

ስሞታህን ለክቡር ሰው ማሰሞትህ የግድ ነው

**አምስተኛው ነጥብ፡ *ይህ ሐሳብ እና ትካዜ ከአላህ ﷻ የመጣ ፈተና መሆኑን ማወቅ።***

ሐሳብ እና ትካዜን አላህ ﷻ የሰውዬውን ደረጃ ከፍ ለማድረግ ምክንያት አድርጎታል። ሐሰኑልበስሪ እንደትናገሩት *“አንድ ሰው የቂያማ እለት በመልካም ስራው መዝገብ ላይ ከሚያገኛቸው መልካም ነገሮች እጅግ ታላቁ በዱንያ ያጋጠመው ሐሳብና ትካዜ ነው።”* አላህ ﷻ የብዙ አማኞችን ደረጃ ከፍ የሚያደርገው፣ የቂያማ ቀንም ደረጃቸውን የሚያልቀው በዱንያ እያሉ በሚያጋጥማቸው ሐሳብና ትካዜ ነው። ለዚህም ነው የአላህ መልእክተኛ ባልደረቦች፣ በል እንዲያውም የአላህ ነብያት በአደጋ የሚደሰቱት። ከአቡ ሰዒድ አል-ኹድሪ እንደተዘገበው *“በነብዩ ﷺ ላይ ገባሁና እጄን እርሳቸው ላይ አስቀመጥኩ፣ ከተሸፈኑበት ልብስ በላይ ያለው የሰውነታቸው ትኩሳት ተሰማኝ። ከዛም*

*ለነብዩ ﷺ 'የአላህ መልክተኛ ሆይ! በርግጥም ታተኩሳለህ (በህመም)?' አልኳቸው፤ እሳቸውም* ***«ከእናንተ ሁለት ሰዎች የሚያተኩሱትን ያክል እያተኮስኩ ነው»*** *አሉ። ከዛም አቡ ሰዒድ "እናንተ በስጦታ ከምተደሰቱት በላይ እነሱ (ነብዩ ﷺ ባልደረቦቻቸው) በአደጋ ይደሰቱ ነበር"* ብሎ ተናገረ።" የዚች የአቡ ሰዒድ ንግግር መልእክት ነብያት በአደጋ ጊዜ ሰዎች በሰጦታ ከሚደሰቱት በላይ ይደሰታሉ ማለት ነው። የአላህ መልእክተኛ ባልደረቦችና ደጋግ የአላህ ﷻ ባሮች በሰጦታ ከሚደሰቱት የበለጠ በአደጋ ይደሰታሉ። ምክንያቱም የሰው ልጅ የቂያማ ቀን ሰላት፣ ጾምና ሰደቃ በማብዛት የማያገኘውን ደረጃ አላህ ﷻ በእርሱ ላይ ባደረሰበት አደጋ ያገኛል። ከነዚህ አደጋዎች ደግሞ ሐሳብ እና ትካዜ ይካተታሉ።

ስለዚህ: እነዚህ ከላይ ያሳለፍናቸው አምስቱ ነጥቦች አንድ ሰው ይህንን ችግር ቀላል የሚአያደርግባቸው መፍትሄዎች ናቸው። ከሌሎቹ በበለጠ እርሱን እንዲቀለው ያደርጋሉ። ነገር ግን አንድ ሰው ማወቅ ያለበት ይህ አደጋና ሐሳብ ሙሉ በሙሉ አይወገድም። ሰዎች ሁሉ የተለያዩ ናችው እንጂ ማንኛውም ሰው ላይ መከሰቱ አይቀሬ ነው። አንድ አንድ ሰው ታላላቅ ነገራቶችን አሳንሶ ይመለከታል። እናም ታላቅ ጉዳዮች በሚመጡበት ጊዜ ትንሽ ነው የሚያሳስበው። ሌላው ሰው ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ ነው። ተንሽ ነገር ሲያሳስበው በነፍሱ ላይ ከተራራ በላይ ይከብድበታል። ለዚህም የመጀመሪያው ምክንያት በአላህ ﷻ አለማመኑ ሲሆን፤ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ነገራቶችን በተገቢው ቦታቸው አለማስቀመጡ ነው። ለዚህም አንድ አንድ ሰዎች የተጠጨነቁና የጠበባቸው ሆነው ታገኛቸዋለህ፤ ነገር ግን ወደ ጉዳያቸው ስትመለከት ጉዳዩ እጅግ ቀላል ሆኖ ታገኘዋለህ። ነገር ግን ነገራቶቹን አክብዶ ስላያቸው ነው።

አቡ አጥ-ጠይብ አል-ሙተነቢ እንዳለው:

.............................................. *** ትንንሾች ተንንሽ ሰዎች ጋ ይገዝፋሉ

ስለዚህ ዋናው ነጥብ: ሐሳብ በሁሉም ሰው ላይ መከሰቱ ነው። አንድ አንድ ሰው በዲኑ ጠንካራ ከሆነ ምንም አይነት ሐሳብና ትካዜ የማያጋጥመው ይመስለዋል። ይህ ትክክል አይደለም። አላህ ﷻ በቁርአኑ እንዲህ ይላል:

﴿مَنۡ عَمِلَ صَٰلِحٗا مِّن ذَكَرٍ أَوۡ أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤۡمِنٞ فَلَنُحۡيِيَنَّهُۥ حَيَوٰةٗ طَيِّبَةٗۖ﴾

*﴿ከወንድም ሆነ ከሴት እርሱ አማኝ ሆኖ በጎን የሰራ በርገጥም መልካም ኑሮን እናኖረዋለን﴾* [አል_ነሕል፡97] ማለቱ ሰውዬ በዱንያ ላይ ብዙ ገንዘብ በማገኘት፣ ብዙ ልጆችን በማግኘትና ሐሳብና ትካዜ በመወገድ እድለኛ ይሆናል ማለት አይደለም። ነገር ግን መልእክቱ በዚች ዱንያ ላይ ባለበት ሁኔታ ላይ ሆኖ ደስተኛ መሆን ማለት ነው። ከገንዘብ ወይም ከልጅ ወይም ከጤና የሆነ ነገር ሲጎድለበት የአላህን ﷻ ውሳኔ ይወዳል። በዛም ነፍሱ ትረጋጋለች፤ እናም መልካም እድል ይሆንለታል ማለት ነው። ሐሳብና ትካዜ በሚያጋጥመው ጊዜ የአላህ ﷻ ውሳኔ መሆኑን ያውቃል፤ ነፍሱም ትረጋጋለች። ሌሎች ሰዎች እንደሚጨናነቁት አይጨናነቅም። አንድ አንድ ሰው ትንሽ አደጋ ባጋጠመው ጊዜ እንዲህውም ሐሳብና ትካዜ በመጣበት ጊዜ፣ ከአላህ ﷻ ይርቅና አላህ ﷻ ከዚህ አደጋ መውጫ ምክንያት ያላደረገውን ነገር በመጠቀም ከአደጋው መውጣት ይፈልጋል። ከራሱ ላይ ሐሳቡንና ትካዜውን ለማጥፋት አእምሮውን የሚሸፍን ነገር ይጠጣል፤ ወይም ብዙ ዛዛታ ወሬ ወዳለበት ቦታ ይሄዳል። በዚህ ድርጊቱም አላህን ያስቆጣል። እውነታው ግን በእሳት ላይ ነዳጅ እያፈሰሰ ነው። አእምሮውን ከሸፈነለትም ለትንሽ ቆይታ ብቻ ነው። አእምሮው ወደ ትክክለኛው ሁኔታው ሲመለስ የነበረውን ነገር እንዳለ ያገኘዋል፤ ነፍሱ ግን ከአላህ ﷻ መራቅን ጨምራለች። በዚህ ጊዜ ሐሳቡ ሌላ ሐሳብ ይጨምርበታል። አማኝ የሆነ ሰው ሐሳብና ጭንቀት የሌለው አገር የመጨረሻው አገር እንደሆነ ያውቃል። በርግጥም አላህ ﷻ ስለ አማኞች ሲናገር ጀነት በገቡ ጊዜ፡

﴿وَقَالُواْ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ ٱلَّذِيٓ أَذۡهَبَ عَنَّا ٱلۡحَزَنَۖ﴾

*“ምስጋና ለዚያ ከእኛላይ ሐዘንን ላስወገደልን አላህ ይገባው።”* እንደሚሉ ነግሮናል።

ዱንያ ባጠቃላይ ሐዘን ነች። በሐዘንም ላይ ነው የተፈጠረችው።

ማሊክ ኢብኑ ረይብ ስለ ዱንያ ሲናገር እንዳለው፡

በመጽዳት፣ በመጥራት ላይ ስትጠብቃት

### በመደፍረስ፣ በመቆሸሽ ተፈጥራለች

በመጨረሻው ቀን ጀነት ውስጥ ሐዘን የሚባል የለም። ሐሳብም ጭንቀትም የለም። አላህ ﷻ በጀነት ሰዎች ላይ በመጽሐፉ ከዋለላቸው ጸጋዎች አንዱ የቂያማ እለት ሐዘንን ከነሱ ላይ ማስወገዱ ነው።

ስለዚህ፡ አንድ አማኝ የሆነ ሰው ከሐሳብና ከትካዜ የሆነ ነገር ካጋጠመው በአላህ ﷻ ሸሪዓ ላይ በመጣው በእርሱ ውሳኔ በማመን፣ የአላህን መጽሐፍ ማንበብ በማብዛት፣ እርሱን በመለመንና መልካም ስራዎችን በመሰራት ወደሱ በመቃረብ ይቀንሰዋል።

እጅግ ግሩም በሆነው በነብዩ ﷺ ሐዲሥ ንግግሬን ልቋጭ። ይህም ሐዲሥ ኢማሙ አሕመድ እና ጦበራኒ እንደዘገቡት ነብዩ ﷺ ***«በአላህ መንገድ ላይ ታገሉ፤ እርሱ (መልካም ስራ) አላህ ﷻ ሐሳብና ትካዜን ያስወግዳል።»*** ብልዋል። በአላህ ﷻ መንገድ ላይ መታገል መገዳደል ብቻ አይደለም። መታገል ሲባል የራስን ነፍስያ መታገል፣ የሌሊት ሰላት በመስገድ፣ የአላህን መጽሐፍ በማንበብ እና እውቀት በመፈለግ ነፍሱን ይታገላታል። አቡ አድ-ደርዳእ አንድን እውቀት ፈላጊ ሰው በተመለከተ ጊዜ *"እነዚህ ሁለት እግሮች ይደሰቱ፤ እነርሱ በአላህ ﷻ መንገድ ላይ ነው አቧራ የለበሱት። ነብዩ ﷺ* ***«እውቀትን ፈልጎ መንገድን የተጓዘ አላህ ﷻ የጀነትን መንገድ ያገራለታል»*** *ሲሉ ሰምቻለሁ።"* ይላል። አላህን በመታዘዝ ላይ ነፍሱን የታገለ ሰው አላህ ﷻ ከእርሱ ላይ ሐሳብንና ትካዜን ያስወግደለታል። ለዚህም ነው ኢብራሂም ኢብኑ አድህም *"እኛ አላህን በመታዘዝ ላይ ያለንበትን ጸጋ የነገስታት ልጆች ቢያውቁ ኖሮ በሰይፍ ይፋለሙን ነበር።"* የሚሉት። ተማሪያቸውም ሱፍያን ኢብኑ ሰዕድ አሥ-ሠውሪ *"እኛ እውቀትን በመፈለግ የምናገኘውን ጸጋ ወይም ጣእም የሀብታም ልጆች ቢያውቁ ኖሮ እጅግ በጣም ውድ በሆነ ዋጋ ይገዙን ነበር።"* ይላሉ። ይህ የሆነበት ምክንያት አንድ ሰው አላህን በመታዘዙ ሌላ ጣዕም የማይወዳደረው ጣዕም፣ ሌላ ደስታ የማይወዳደረው ደስታ ያገኛል። ነገር ግን ይህ የሚሆነው ከአላህ ﷻ ጋር እውነተኛ ግንኙነት ላለው ሰው ነው። ሓኪም እና አሕመድ ከኢብኑ መስዑድ እንደዘገቡት የአላህ መልእክተኛ **« አላህ ﷻ የከለከልውን ነገር መፈጸም እየቻለ አላህ ﷻ ዘንድ ያለውን (ምንዳ) ፈልጎ ወደዛ መመልከት የተወ ሰው**

**አላህ ﷻ በልቡ ውስጥ የኢማን ጥፍጥናን ይተካለታል።»** ብለዋል። የኢማንን ጥፍጥና ያገኘ ደግሞ በዱንያ ሁሉም አይነት ፈተና እና ጭንቀት ይቀልለታል።

ታላቁን ጌታችንን አላህ ﷻ፣ የተከበረው የዐርሽ ጌታ የሆነውን አምላክ ለሁላችንም ቅናቻና እርሱን ፍራቻ እንዲለግሰን እማጸነዋለሁ፤ ጠቃሚ እውቀትና መልካም ስራ እንዲለግሰን እለምነዋለሁ። አላህ ﷻ ከእኛ ላይ ሐሳብና ትካዜን እንዲያስወግድልን እለምነዋለሁ፤ ከኛም ላይ ወንጀሎቻችንን እንዲምርልን፣ መጥፎ ምግባሮቻችንን እንዲያብስልንና ለኛም ለወንድም፣ ለሴትም አማኞች እንዲምር እለምነዋለሁ።

አላህ በነብያችን ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው በሙሉ ሰላትን ያውርድ።